# ህዝበ ሙስሊሙ ከጽንፈኝነት ምን ይጠቀማል?

ከስኢድ መሐመድ

የተለያዩ ጸሃፊያንና ምሁራን ኢትዮጵያን በሚመለከት በተለያየ ወቅት ካሚያነሷቸው ነገሮች መካከል ኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ልዩነት በአብሮነታቸው ላይ የፈጠረባቸው አንዳችም ችግር አለመኖሩን ነው፡፡ በመላው ዓለም ከሚገኙ አገራት ጋር በንጽጽር ሲታይ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ያለው የሃይማኖት መቻቻልና የጠበቀ ወንድማማችነት ለዘመናት በአርአያነት ሲጠቀስ ኖሯል፡፡

በአገሪቱ የሚገኙ ከሰማኒያ በላይ ብሄር ብሄረሰቦ'ችና ህዝቦች ተግባብተውና ተሳስበው መኖራቸው፤ ብዝሃነታቸው ውበታቸው መሆኑን በመገንዘብ በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነታቸውን በማጽናት የአገራቸውን ሉአላዊነት በማስከበር በነጻነት የሚኖሩ ህዝቦች ለመሆናቸው በርካታ ደራሲያን የመሰከሩት ጉዳይ ነው፡፡ ይህ አገር ያወቀው ጸሃይ የሞቀው ጉዳይ ስለምን ማንሳት ተፈለገ? ትሉ ይሆናል፡፡

ለዘመናት የዘለቀውን የሃይማኖት መቻቻልና ወንድማማችነት ለማናጋት እየተፈጠረ ያለው የወቅቱ ሃይማኖት ለበስ የፖለቲካ ሴራ፣በህዝበ ሙስሊሙ በአጠቃላይም በህብረተሰቡ ላይ እያስከተለ ያለው ችግር ለማንሳት ያህል ነው፡፡

የአገራችንን ልማት ለማደናቀፍ፣ ሰላሟን ለማደፍረስ፣ ህዝቦቿን በአንድም ይሁን በሌላ መልክ ለመከፋፈልና ወደ እርስ በርስ ደም መፋሰስ ለማስገባት ያልተፈነቀለ ድንጋይ ያልተበጠሰ ቅጠል የለም፡፡ የአገሪቱ የልማት፣ የሰላምና የዴሞክራሲ ጅምር የጸና መሰረት ላይ የቆመ በመሆኑና በተለያየ ሃይማኖት ተከታዮች መካከልም ያለው አንድነትና ወንድማማችነት ስር የሰደደ በመሆኑና በሴረኞች ሊሸረሸር ባለመቻሉ ግን አሁንም አንድነታችንንና ሰላማችንን ጠብቀን እየተጓዝን እንገኛለን፡፡

እንደሚታወቀው ሁሉ ቀደም ሲል በተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል ብጥብጥና ሁከትን ለመፍጠር አቅደው ረጅም መንገድ የተጓዙ የፖለቲካ ቡድኖች ነበሩ፡፡ ህዝብን የመከፋፈልና አንድን ብሄር በሌላው ላይ በማነሳሳትና ብጥብጥና ሁከት ለመፍጠር አቅደው ነበር የተንቀሳቀሱት፡፡ይህን መሰሉ እኩይ ተግባራቸው ሙሉ በሙሉ ባይሳካም የተወሰነ ጫናና ጉዳት አላሳደረም ማለት ግን አይቻልም፡፡

የፖለቲካው እንቅስቃሴና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚያነሱት የብጥብጥ አጀንዳ ባልተሳካበት ወቅትም እጃቸውን አጣጥፈው አልተቀመጡም፡፡ ለምድ ለብሰው በሌላ መልክ ብቅ አሉ እንጂ፡፡ መጀመሪያ የአንድ ሃይማኖት አማኞችን በሌላ ሃይማኖት አማኞች ላይ በማነሳሳት የሃይማኖት ጦርነት

በአገራችን ውስጥ ለማስነሳት መሄድ የቻሉትን እርቀት ያህል ተጉዘዋል፡፡ አንዳንድ በዚሁ ሃይማኖት ለበስ የፖለቲካ አጀንዳ የተታለሉ ሰዎችና የእንቅስቃሴው ባለቤት አባላት የሆኑ ግለሰቦችም በአንዳንድ የሃይማኖት ስፍራ እየገቡ የብጥብጥና የሁከት መነሻ የሆኑ እርምጃዎችን ወስደዋል፡፡

ለዚህ ትልቅ ማሳያ የሚሆነውም የሃይማኖት በዓላት የሚከበሩባቸው ቀናትን እየቆጠሩ አማኞች ሃይማኖታዊ ተልእኮአቸውን ለመወጣት በሚሰበሰቡበት ስፍራ ሰርገው በመግባት ብጥብጥ ለመፍጠር ያላደረጉት ጥረት አልነበረም፡፡ ይሁንና የሕግ የበላይነትን ለማስከበርና የዜጎችን ነጻነትና ሰላም ለመጠበቅ በመንግሥትና በህብረተሰቡ የተቀናጀ እርምጃ የታቀደው ዓላማ ጸረ ሰላም ኃይሎች እንደፈለጉት ባይሳካም ገጽታውን እየለዋወጠ መምጣቱ ግን አልቀረም፡፡

ባለፉት ጥቂት ወራት በህዝበ ሙስሊሙ መካከል እየሰፋ የመጣው መከፋፈልና የእርስ በርስ ግጭትም የዚሁ አንድ ገጽታ ነው፡፡ የዚህ ክፍፍልና ግጭት መሰረት ምንድን ነው? ጉዳዩ የማን ጉዳይ ነው? በዚህ ክስተት ላይ የመንግስት ሚና ምን መምሰል ይኖርበታል? ይህ ግጭትና ደም መፋሰስ ለህዝበ ሙስሊሙ ምን ይፈይዳል? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ በዚህ የጽንፈኝነት እንቅስቃሴ ላይ አንድ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያግዛል፡፡

ቀደም ሲል በጥቅሉ እንደተገለጸው ኢትዮጵያውያን ካሏቸው እሴቶችና የሚያኮሩ ባህሎች መካከል በተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል ያለው መቻቻልና ወንድማማችነት ነው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ደግሞ ለሌሎች ያላቸው ርህራሄ ከፍርሃ ፈጣሪ የመነጨና ለዘመናት አብሯቸው የዘለቀ መሆኑ ነው፡፡ በውስጣቸው ሰላምን በማስረጽ የእርስ በርስ መዋደድ፣ መተጋገዝና መረዳዳትን በማስፈን በአገሪቱ ከሚገኙ የሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ጋር በቅንነት የፈጣሪያቸውን ትእዛዝ በሚፈቅደው መሰረት በመቻቻልና በመከባበር ለመኖር የሚያስችል ትዕግስትና ውስጣዊ ሰላም የሰነቁ መሆናቸው ነው፡፡ በዚህ ረገድ በአገሪቱ ባሉት የተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል መቻቻል እንዲኖር የሙስሊሙ ህብረተሰብ ድርሻ በእጅጉ የጎላ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡

የህዝበ ሙስሊሙ የችግርና የግጭት አፈታት ባህልም ሌላው እሴት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ግጭትን ከመፍጠር የተቆጠቡ ሰላምን የሚመኙ ለሰላም የሚቆሙ ዜጎች ናቸው፡፡ ሆኖም ግን በተለያየ ምክንያት ግጭት በሚፈጠርበት ወቅትም ችግሮቹን በውይይትና በሰላማዊ መንገድ በመፍታት ረገድ ከፍተኛ ተሞክሮ አላቸው፡፡ ለሌሎች ሰዎች ያላቸው ርህራሄም ሌላው የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ሃይማኖታዊ ተልዕኮው ነው፡፡ በተጨባጭ እንደሚታወቀው ህዝበ ሙስሊሙ ሃይማኖታዊ በዓላቱን በሚያከብርበት ወቅት ከሌሎች የሃይማኖት ተከታይ ጎረቤቶቹና ወዳጆቹ ጋር በደስታ ማሳለፉ ብቻ ሳይሆን የተቸገሩ ወገኖቹን በማሰብና በዓሉን በደስታ እንዲያከብሩ በማድረግ ርህራሄውን ይገልጻል፡፡

ከላይ ያነሳኋቸው ነገሮች ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ለዘመናት ይዘዋቸው ከዘለቁት መልካም ተግባራት መካከል ጥቂቶቹን ናቸው፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ እነዚህን ተግባራት የሚፈጽመው ለሃይማኖቱ ካለው ቀናዒነት የተነሳ ነው፡፡ ይህ የሃይማኖታዊ ቀናኢነት አሁንም ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መነጋገሪያ እየሆነ የመጣው በህዝበ ሙስሊሙ መካከል የተፈጠረው የእርስ በርስ ግጭት ታዲያ መሰረቱ ምንድን ነው? የዚህ ክፍፍልና ግጭት መሰረቱ የጥቂት ግለሰቦችና ቡድኖች ጽንፈኝነት ነው፡፡ ድርጊቱ የህዝበ ሙስሊሙን አንድነትና ሕብረት የሚበትን፣ የእምነት ቀናኢነቱን የሚሸረሽር እኩይ ተግባር እንጂ ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ተልዕኮ የየለውም፡፡

ለዘመናት የዘለቀው የእርስ በርስ መተሳሰብና ወንድማማችነትን ለመበጥበጥና ጭራሽ ወዳልተፈለገ ደምመፋሰስና እልቂት ለማስገባት የታቀደ ነው፡፡ ድርጊቱ ከእርስ በር ደም መፋሰስና እልቂት አልፎም ከሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ጋር ለዘመናት የነበረውን ትስስርና መከባበር የሚያሽመደምድና ወደ ግጭት የሚያስገባ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመላው ህዝብን ሰላም የሚያናጋ ተግባር ነው፡፡ በህዝብ መካከል የሚፈጠር ማንኛውም ዓይነት ግጭት ውጤቱ የከፋ ቢሆንም ከሃይማኖትና በሃይማኖት ሰበብ የሚነሳ ግጭት ግን ከሁሉም የከፋ መሆኑ የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ግጭት ለልጅ ልጅ የሚተርፍ፣ ጠባሳው የማይሽርና መቋጫ የለሽ ነው፡፡

ጥቂት ሰዎች የእስልምናን ሃይማኖትን በማስታከክ እያደረጉት ያለው እንቅስቃሴ መሰረቱ በጽንፈኝነትና አክራሪነት የተለወሰ የፖለቲካ አጀንዳ ለመሆኑ የሚያጠራጥር ነገር የለም፡፡ አክራሪዎቹ ከአልቃይዳ፣ ከአልሸባብና ከሌሎች አሸባሪ ቡድኖች ጋር የጠበቀ ግንኙነትን በመመስረት የገንዘብና ሌሎች ድጋፎችን በማሰባሰብ የህዝበ ሙስሊሙን ሰላም የማወክ ተልእኮ አንግበው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ናቸው፡፡ ይህ ጸረ ሰላም ቡድን የውጭ ድጋፍ እንዳለው ሌላው ማረጋገጫ ደግሞ በቅርብ ጊዜ የተፈጠረውን የውጭ ዜጎች ጣልቃ ገብነትን ማየት ብቻ በቂ ይሆናል፡፡ ከውጭ የመጡ ዜጎች ወደ ኢትዮጵያ በሕጋዊ መንገድ ከገቡ በኋላ ቀጥታ ወደ አንዋር መስጊድ በመሄድ የብጥብጥ ተልእኮ ያዘሉ መልእክቶችን በመበተን ላይ እንዳሉ እጅ ከፈንጅ መያዛቸው ይታወቃል፡፡ እንዴት ኢትዮጵያ ውስጥ ብጥብጥ አዘል ወረቀት ለመበተን ከውጭ ሊመጡ ቻሉ? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ግልጽ ነው፡፡ በህዝበ ሙስሊሙ መካከል የተፈጠረው ክፍፍልና ግጭት በውጭ የሚገኙ ፖለቲከኞችና አክራሪዎች ሊጠቀሙበት አቅደው እንደጀመሩትና ይህንኑ ወደከፋ ደረጃ ለማድረስ አሁንም እየገፉበት ያሉ መሆናቸው ነው፡፡

ይህ አገራችን ላይ የብጥብጥና የሁከት ፍታውራሪ የሆነው ቡድን በዓለም ደረጃ በተለያዩ አገራት ከሚንቀሳቀሱ ጽንፈኞች ጋር ግንኙነትን በመመስረት በኢትዮጵያ ያለውን የሃይማኖት ሰላም ለማወክ

የተነሳ ቡድን አካል ነው፡፡ ስለዚህ መሰረቱ ትምህክትና ጽንፈኝነት ነው፡፡ በምድር ላይ ከእኔ የእኔን ሃይማኖት ከሚከተሉ በስተቀር ሌላ ሰውና ሃይማኖት መኖር የለበትም የሚል መርህን የያዘ ነው፡፡ አገራት በሃይማኖታዊ መንግስት መመራት አለባቸው፤ በዚህ መሰረት ደግሞ በአገራችን የእስልምና ሃይማኖታዊ መንግስት መመስረት አለበት የሚል ዓላማ ይዟል፡፡ የአንድ ሃይማኖት የበላይነት የሚሰበክባትና አንድ ሃይማኖታዊ እምነት ብቻ የሚኖራት አገር የመፈለጉ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ህዝቡ በሕገመንግስት የተሰጠውን የሃይማኖት ነጻነት የሚጋፋ በመሆኑ ሕጋዊነት የጎደለው ጸረ ዴሞክራሲ አካሄድ ነው፡፡

እንቅስቃሴው በዋናነት እየተመራ ያለው ህቡእ የፖለቲካ ተልኮ ባላቸው ግለሰቦች ነው፡፡ ይህ ሃይማኖታዊ ተልእኮ የሌለው አጀንዳ ህዝበ ሙስሊሙን ለግጭትና ለደም መፋሰስ እየዳረገው ይገኛል፡፡ በዚህ ሁከት ህዝበ ሙስሊሙ ቀዳሚ ተጎጂ ከመሆኑ በስተቀር የሚያገኘው አንዳችም ጠቀሜታ አይኖርም፡፡ ከዚህም በላይ ይህ ሕገመንግስቱን ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለመናድና የአገሪቱን ልማት ለማሰናከል ያለመ በመሆኑ፤ መላው ህዝበ ሙስሊም ከመንግስትና ከሌላው ሕብረተሰብ ጎን በመሰለፍ ሊቀጨው ይገባል፡፡

በአገሪቱ ሕግና ስርዓትን ማስከበር፣ የሕግ የበላይነትን መጠበቅ፣ የዜጎች ሰላምን ማረጋገጥ፣ ዜጎች በሰላም ወጥተው የፈለጉትን ዓይነት ስራ ያለመሸማቀቅና በነጻነት አከናውነው መመለስ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር የመንግስት ሃላፊነት ነው፡፡ መንግስት ደግሞ ይህንን ሃላፊነቱን በብቃት የሚወጣው የመላው ሕብረተሰብ ድጋፍና ርብርብ ሲታከልበት ነው፡፡
የዚህ መከፋፈልና ግጭት መዳረሻው እሩቅ ነው፡፡ ዋና መዳረሻው ግጭቱን መጀመሪያ በሙስሊሙ ሕብረተሰብ፣ ከዚያም በተያዩ ሃይማኖቶች መካከል በማስፋት መንግስት ሰላምን ለማስጠበቅ የሚያደርገውን ጥረት የሃይማኖት ረገጣ፣ የሃይማኖት አፈናና በመሳሰሉ ሌሎች ቃላትና ሓረጎች በመጠቀም በህዝብና በመንግስት መካከልም ያለውን ግንኙነት በማሻከር፤ ቅራኔና ፍጅትን በመፍጠር ህቡእ የፖለቲካ አጀንዳን ሕገወጥ በሆነ መንገድ ማስፈጸም ነው፡፡

በአገራችን በተፈጠረው ሰፊ የፖለቲካ ውቅያኖስ በተገቢው መንገድ መዋኘት ያልቻሉ አንዳንድ ጽንፈኛ ፖለቲከኞች ህዝቡ ባለፉት ምርጫዎች አንቅሮ የተፋቸው በመሆኑ በበቀል ስሜት ተነሳስተው ህዝቡን እርስ በርሱ ለማፋጀትና ለደም መፋሰስ ለመዳረግ እየተንቀሳቀሱ ነው፡፡ ህዝቡን እርስ በርስ በማጋጨት ለማያባራ ደምመፋሰስ መዳረግና የአገሪቱን ሰላም በማደፍረስ መንግስት ሰላምን ለማስከበር ሊወስደው የሚችለውን እርምጃ እያወነጋገሩ በማቅረብ አገሪቱ ውስጥ የሃይማኖት ነጻነት ጠፋ፣ መንግስት ይህንን መቆጣጠር አልቻለምና የመሳሰሉትን ሐሳቦች በተለያዩ ሚዲያዎች በማስተጋባት ህዝቡ መንግስት ላይ ያለው እምነት እንዲሸረሸር ለማድረግ ከንቱ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

በዚህ መልኩም ጽንፈኞችንና የኢትዮጵያን ልማት ማየት የሚያማቸውን ሰዎችና ቡድኖችን እንደ አምላክ እየሳሉ በአገራችን እየመጣ ያለውን ሁለንተናዊ ለውጥ እያጥላሉ የመዘገብ አባዜ የተጠናወታቸው አንዳንድ የግል ሚዲያዎችም ሁኔታውን በማራገብ የጸረ ሰላም ኃይሎች አፈቀላጤ ሆነው ቀርበዋል፡፡ በህዝብ ዘንድ ውዥንብርን በመፍጠር ምናልባት በግርግሩ ሰበብ ወደ ህዝብ መግቢያ ቀዳዳ መፈለግ ሌላው የእነዚህ የከሰሩ ፖለቲከኞች እቅድ ነው፡፡ እነዚህ በሃይማኖት ሽፋን በመንሳቀስ ላይ ያሉት ቡድኖች ቀደም ሲል በፖለቲካው ሜዳ መወዳደር ሳይችሉ ቀርተው የኢትዮጵያ ህዝብ አንቅሮ የተፋቸው ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡ አንደኛው የተቀደሰው የእስልምና ሃይማኖት ስለምን ለከሰሩ ፖለቲከኞች መጠጊያና መጠቀሚያ ይሆናል? የሚል ሲሆን ሌላው ደግሞ ህዝበ ሙስሊሙ ከዚህ የብጥብጥና የእርስ በርስ ደም መፋሰስ የሚያገኘው ፋይዳ ምንድን ነው? የሚል ይሆናል፡፡

ማንም ሰው ከግጭት ተጠቃሚ እንደማይሆን ያደባባይ ምስጢር ነው፡፡ በማንኛውም መስፈርት ወደ ግጭት የገቡ ወገኖች ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ የሚሆኑበት አጋጣሚ አይኖርም፡፡ እርግጥ ነው ነጻነት በሌለበት አገር ይህ ነገር ቢነሳ ላያከራክር ይችላል፡፡ የህግ የበላይነት ባልተከበረበትና ዴሞክራሲ ባልሰፈነበት የአፈና ስርዓት ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች ይህንን ቢያነሱት ትክክለኛ አማራጭ ነው፡፡ የዜጎች እኩልነት ባልተረጋገጠበት፣ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት በሚጣስበት አገር ቢነሳ ተገቢነቱ ጎልቶ ይወጣል፡፡ ነገር ግን በዚች የሃይማኖት ነጻነት የተረጋገጠባት፣ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት እውን በሆነባት፣ ሰላምና ዴሞክራሲ በሰፈነባት እና በእድገት ምህዋር በምትሽከረከር አገር ይህ ክስተት ሊከሰት ሁለንተናዊ ገጽታው ባልፈቀደ ነበር፡፡ ይሁንና ልማትን የሚጠሉ ውድቀትን የሚያቀነቅኑ ቡድኖች እስካሉ ድረስ አገሪቱን ወደኋላ ለመመለስ መፍጨርጨራቸው አይቀርም፡፡

ህዝበ ሙስሊሙ በአገራችን እንዳሉት ሌሎች የሃይማኖት አማኞች ሁሉ የእምነት ነጻነቱ ከተረጋጠ ከሁለት ዓሰርት ዓመታት በላይ ተቆጥሯል፡፡ ከዚያ በፊት በአገራችን የነበረው ሁኔታ ማንም የሚረሳው አይደለም፡፡ የሃይማኖት ነጻነታችን ተነፍገን 'አላህ አክበር!' አለያም 'እግዚአብሔር ይመስገን' በማለት ፈንታ 'ኢትዮጵያ ትቅደም!' እንድንል ተገደን የነበርንበት ወቅት የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ የጸሎት ስፍራዎች እየተቃጠሉና ሃይማኖታዊ ቅርሶቻችን እየተዘረፉ እያየን ለምን? ብሎ መጠየቅ እንኳን በማይቻልበት የአፈና ስርዓት ማለፋችን ሁሉም የሚያውቀው ሃቅ ነው፡፡ በቀደሙት ስርዓታት የነበረው የሃይማኖት ነጻነት ችግር ታሪክ ከሆነ በርካታ ዓመታት አልፈዋል፡፡ ይህን በአላህ ፊት ቆመን ለነፍሳችን ስንል የምንመሰክረው ሃቅ ነው፡፡

ቀደም ሲል የነበሩት ጥቂት የእምነት ስፍራዎች ህዝበ ሙስሊሙ በሚፈልገው መጠን ተስፋፍተዋል፡፡ አንዳንድ እምነቶችን በተመለከተም በጸሎት ስፍራዎች ተሰባስቦ መገኘትም ይሰጠው በነበረው የተዛባ ትርጉም ምክንያት ብዙዎች ሃይማኖታቸውን በነጻነት እንዳያመልኩ ተደርገው የነበረበትን ሁኔታ እዚህ ላይ ማስታወሱም ተገቢ ነው፡፡

ዜጎች ሃይማኖታቸውን በሚመለከት የሚያደርጉትን መሰባሰብ ሌላ የፖለቲካ ትርጉም እየተሰጠው በርካታ ወንድሞቻችን 'ከብት ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" እንዲሉ የፖለቲካ ሴረኞች በሚል ለህልፈተ ህይወት ተዳርገዋል፡፡ በግፍ ተገድለዋል፡፡ ቁጥራቸውን ለማወቅ የሚታክት ሌሎች ዜጎችም ለግርፋት፣ ለእስርና ስቃይ ተዳርገዋል፡፡ የነበረውን ገጽታ በትንሹ ብቻ አስታውሶ ለማለፍ እንጂ ሰቆቃው ተዘርዝሮ የሚያልቅ ሆኖ አይደለም፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ አሁን በኢተዮጵያ ስለሃይማኖት ነጻነት የሚወራበት ወቅት አይደለም፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችል ጥያቄና ለእንደዚህ ዓነት መከፋፈልና ግጭት የሚዳርግ ሁኔታም የለም፡፡ በአገሪቱ ያለው ተጨባጭ ሁኔታ ለእንደዚህ ዓይነት ነገር ምቹነት የለውም፡፡ ከዚህ በመነሳት እየታየ ያለው ክስተት ሃይማኖታዊ ተልእኮ እንደሌለው ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ እስካሁን በተለያየ ጊዜ የቀረቡ አግባብነት ያላቸው የሙስሊሙ ህብረተሰብ ጥያቄዎች ባግባቡ ተመልሰዋል፡፡ ለወደፊቱም ሌሎች ጥያቄዎች ቢኖሩ የመጅሊሱ ሕጋዊ አሰራር በሚፈቅደው መሰረት በሰላማዊ መንገድና በሰለጠነ አካሄድ ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የምናቀርበው ጥያቄ በትክክል ሃይማኖታዊነት ያለውና ሕገመንግስቱ የሰጠንን መብት ተንተርሶ እስከሆነ ድረስ በሚመለከተው አካል በአግባቡ የማይፈጸምበት ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡

መላው የኢትዮጵያ ሙስሊም ሕገመንግስቱ የሰጠው የሃይማኖት ነጻነትና እኩልነት ተከብሮለት እየኖረ ነው፡፡ እምነቱ የሚጠይቀውን ተግባር ሁሉ በነጻነት እያከናወነ ነው፡፡ ለዚህ ምንም አይነት ተጽእኖ እንደማይደርስበትም የሁሉም እምነት ነው፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ክፍሎች በሚያደርጓቸው ነጻ ውይይቶች ላይ እየገጹ ያሉትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡

በወሎ በኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች ከሙስሊሙ ሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር ይህንን አስመልክቶ ከተደረጉ ውይይቶች ላይ ለማወቅ እንደተቻለው መንግስት ሕግን የማስከበር ድርሻውን እንዲወጣ የሚጠይቅ ነው፡፡ በሙስሊሙ መካከል መከፋፈል፣ ብጥብጥና ሁከት እየፈጠሩ ያሉት ጥቂት ግለሰቦች ሃይማኖታዊ ተልእኮ እንደሌላቸውና ህቡእ አጀንዳቸውን ለመፈጸም ዓልመው እየተንቀሳቀሱ በመሆኑ መላው ሙስሊም በሃይማኖቱ ስም የሚነግዱትን ፖለቲከኞች ከመንግስትና ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በመተባበር ለሕግ እንደሚያቀርባቸውም ቃል እየገባ ይገኛል፡፡

የአገራችን ሕገመንግስት ላይ በግልጽ እንደሰፈረው 'መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ አይገባም ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ አይገባም'፡፡ ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም ወይም አማኝ ሃይማኖታዊ ተልእኮውን ለመወጣት በሚያደርገው ማንኛውም አይነት ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ መንግስት አይገድበውም፡፡ ሙሉ የሃይማኖት ነጻነቱ ተረጋግጧል ማለት ነው፡፡

ሆኖም ግን እኛ ሃይማኖታዊ እምነታችንን ለማራመድ በሚናደርገው ማንኛውም እንቅስቃሴና ተግባር መንግስት የሃይማኖት ነጻነታችንን የሚጋፋ ተግባር መፈጸምና ጣልቃ መግባት የለበትም ማለት ጽንፈኞች ሃይማኖታችንን ለመበረዝና ህዝበ ሙስሊሙን ደም ለማፋሰስ እያደረጉ ያለውን ሕገወጥ ተግባር በዝምታ ያያል ማለት አይደለም፡፡ የህዝበ ሙስሊሙም ሆነ የሌላው ሕብረተሰብ ሰላምን የሚያውክ ተግባርን እያየ በዝምታ ይመለከታል ማለት አይደለም፡፡

'እኔ ያልኩትን ብቻ ተከተሉ፣ እኔ የማምነውን እምነት ብቻ እመኑ፣ የሌላ እምነት ተከታዮች ከምድረ ገጽ ይጥፉ" በሚል ትምክህተኝነት የሚመራ ቡድን ተልእኮው የአገሪቱ ሕገ መንግስት ለህዝቦች ያጎናጸፈውን መብት መጻረር ነው፡፡ አገሪቱ የአክራሪዎች አሃዳዊ እምነት ተከታዮች ብቻ እንዲኖሩባት ለማድርግ ያለመና ኢትዮጵያ እንደሃገርም ሃይማኖታዊ መንግስት እንደሚያስፈልጋትና ይህ ሃይማኖታዊ መንግስትም የጽንፈኞቹ ሃይማኖት እንደሆነ ይሰብካሉ፡፡

ጽንፈኝነት ለህዝበ ሙስሊሙ ምን ይፈይዳል? ይህ ጽንፈኝነት ህዝበ ሙስሊሙን ለደም መፋሰስ ከመዳረግ የዘለለ ነገር አይፈይድለትም፡፡ ህዝበ ሙስሊሙ ከዚህ ብጥብጥ ተጠቃሚ አለመሆኑን በመገንዘብና አክራሪዎቹ የያዙት አጀንዳ ሃይማኖታቀዊ ተልእኮ እንደሌለው በመረዳት ጽንፈኞችን ከጉያው ነጥሎ በማውጣት ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብና ከመንግስት ጎን ሆኖ ሊንቀሳቀስ ይገባል፡፡